## አስተርጓሚዎች

የመጀመሪያ ቋንቋዎ እንግሊዝኛ ካልሆነ ሠራተኛው አስተርጓሚ መጠቀም ይችላል። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በቋንቋዎ እርዳታ አቅራቢ አገልግሎቶችን ለማግኘት ይረዳል።

## ከእኛ ምን እንደሚጠበቅ

ዓላማችን ሕይወት/ኑሮዎን እንደገና መምራት እንዲችሉ መርዳት ይሆናል። መብት እንዳልዎ እናምናለን።

- ያለስጋትና ረብሻ ለመኖር
- በክብርና ስነስርዓት ለማነጋገር
- ባህል የማይፈቅደውን ነገር ለመቀበልና ፍትሃዊ ያልሆነ እርዳታ ለመቀበል
- ለሚስጢራዊና ለግላዊ የሆኑ ነገሮች [ለርስዎና ለልጆችዎ ደህንነት ለመጠበቅ]
- ከውሳኔ ደረጃ ለመድረስ ለሚሰጥ መረጃ
- ስለርስዎና ልጆችዎ ኑሮ/ሕይወት ውሳኔ ላይ ለመድረስ

ስለምናቀርበው አገልግሎት ምን ዓይነት ግምት እንዳለዎ መነጋገሩ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## ስለሌሎች አገልግሎቶች መማከርት

በቤተሰብ ብጥብጥ ችግር ላጋጠማቸውና ከCALD ሴቶችና ህፃናት ጋር ለሚሠሩ ሌሎች አገልግሎቶች ስለመኖሪያ ቤት ያለውን አማራጭ ሁኔታ ሠራተኛው ማብራሪያ ማቅረብ ይችላል።

## እኛን እንዴት ማነጋገር ስለሚቻል

እርዳታ ወይም መረጃ ከፈለጉ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋት 9am እስከ ከሰዓት በኋላ 5pm ባለው ጊዜ በመደወል የ Intake Worker/ሠራተኛ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ ይሆናል።

**ስልክ ቁጥር፡ 9689 9588**

በቤተሰብ ውስጥ ስለተፈጠረው ብጥብጥ ጉዳይ ልታነጋግርዎ ትችላለች። አስፈላጊ የሆነ መረጃና እርዳታ ለርስዎ በማቅረብ ሊረዳዎ ወደሚችል አገልግሎት ልትመራዎ ስትችል ኪሳራ ለደረሰበት መጠለያ ሠራተኞችንን/CALD Crisis Housing ያከተተ ይሆናል።

## ከሥራ ሰዓት በኋላ እርዳታ

ከሥራ ሰዓት በኋላ በቤተሰብ በአጥብጥ ችግር ደርሶ እርረዳታ ካስፈለግዎ የሴቶች በቤት ውስጥ ግጭት ችግር አገልግሎት ሰጪ/Women's Domestic Violence Crisis Service በስልክ **9373 0123** ወይም **1800 015 188** መደወል ነው።

## ችግር ለደረሰበት ሌሎች የመጠለያ ቤት አገልግሎት

<u>ከብጥብጥ ላመለጡ ሴቶች</u>:

- Women's Domestic Violence Crisis Service, ስልክ ቁጥር 9373 0123
- Immigrant Women's Domestic Violence Crisis Service, ስልክ ቁጥር 9898 3145

<u>እድሜዋ ከ25 ዓመት በላይ ትዳር ለሌላት ሴት</u>:

- Salvation Army Women's Accommodation Support service ስልክ ቁጥር 9372 2488

<u>ለቤተሰብ</u>:

- Werribee Support and Housing Services ስልክ ቁጥር 9742 6452
- Family Crisis Accommodation Service Sunshine ስልክ ቁጥር 9312 5424 Melton ስልክ ቁጥር 9747 7200

Amharic

women's **health** west

# በቤተሰብ ብጥብጥ ምክንያት ለተፈጠረ ችግር መጠለያ ቤት ይፈልጋሉ ወይ?

# የመጀመሪያ ቋንቋዎ ከእንግሊዝኛ የተለየ ነው ወይ?



**ስልክ ቁጥር፡ 9689 9588**

**በቤተሰብ ብጥብጥ ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ሴቶችና ቤተሰባቸው ከሁኔታው ነፃ ሁነው እንዲኖሩ መርዳት።**

# በቤት ውስጥ ደሕንነትዎ የተጠበቀ ይመስልዎታል?



እርስዎን ወይንም ልጆችዎን ለመጉዳትና ማናደድ ማንም ሰው መብት የለውም።

ህፃናት በቀጥታ ከተበደሉ ወይም እርስዎ ሲናደዱ ካዩ ይሰቃያሉ።

ብዙ ዓይነት የቤተሰብ ብጥብጥ አሉ:

**በአካል** – መምታት፣ መርገጥ፣ የሆነ እቃ መወርወር

**በግብረስጋ** – እርስዎ ሳይፈልጉ የግብረስጋ ግንኙነት ለመፈጸም ማስገደድ

**ስሜት በሚነካ** – እርስዎን ወይም ልጆችዎን ለመጉዳት ወይም ልጆቹን እወስዳለሁ በማለት ማስፈራራት

**በስድብ** – ለርስዎ በመጥፎ ስም መጥራት ወይም መራገም

**በማህበራዊ** – እርስዎን ከጓደኞች ወይም ከቤተሰብ ማግለል፣ የት እንደሚሄዱ መቆጣጠር

**በፋይናንስ** – መሰረታዊ የግል ፍላፅትዎን ለማሟላት ገንዘብ አለመስጠት ለምሳሌ፡ ምግብ ወይም የሚከፈል ሂሳብ

**በማድባትና መከታተል** – በተደጋጋሚ መከታተል ወይም በመገናኘት፣ እርስዎን ለመጉዳትና ለማስፈራራት መሞከር

ብዛት ያላቸው የብጥብጥ ዓይነቶች ሕገ-ወጥ ናቸው። ስለዚህ ለፖሊስ መናገር መብትዎ የተጠበቀ ነው።

በቤተሰብዎ ውስጥ ብጥብጥ ካለ ብቻዎን መጋፈጥ አይኖርብዎም፡ መርዳት የሚችሉ አገልግሎቶች አሉ።.

## ችግር/ኪሳራ ለደረሰበት መጠለያ ቤት

ሴቶችና ህፃናት በብጥብጥ ጊዜ ሸሽተው እስከ ስስድስት ሳምንታት የሚቀየበት የመጠለያ ቤቶች በምዕራብ የሴቶች ጤና/Women's Health West በኩል ይቀርባል።

እዚያ በሚቀየበት ጊዜ በባህላዊና ቋንቋ ቅንጅት/ Culturally and Linguistically Diverse (CALD) የችግር መጠለያ ሰራተኞችን ሊረዳዎ ሲችል ከዚያም እርስዎን መርዳት ወደሚችሉ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ያገናኝዎታል።

በዚህ የመጠለያ ቤቶች ክፍት ቦታ ከሌለ የችግር መጠለያ ሰራተኞችን(CALD) እርስዎ ሌላ የመጠለያ ቦታ የሚያገኙበትን ሌሎች መንገዶች በመፈለግ መርዳትና እርስዎን በመወከል ሌሎች አገልግሎቶችን ሊያነጋግር ይችላል።

## እንዴት ልንረዳዎ እንደምንችል

በዚህ መጠለያ ቤት ውስጥ በሚቀየበት ወቀት የCALD ሰራተኞችን በብዙ መንገድ መርዳት ይችላል። ለምሳሌ:

- በማጽናናት መርዳትና ስለሚኖርዎት አማራጭ ሁኔታ መረጃ መስጠት ይሆናል።
- እቅድ እንዲያወጡ በመርዳት እርስዎና ልጆችዎ አሁንም ሆነ ለወደፊቱ ለመኖር ደህንነትዎ የተጠበቀ ይሆናል።
- የሴት ሠራተኛ ከርስዎ ጋር ወደ ፖሊስ በመሄድ ወይም በፍርድ ቤት ሊረዳዎ ከሚችሉ ሌሎች ሠራተኞች ጋር ማገናኘት ይሆናል።
- ለምሳል፡ ከአጠገብዎ እንዳይደርስ የፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲሰጥ ለማመልከት ልትረዳዎ ትችላለች። በዚህ የፍ/ቤት ትእዛዝ ውስጥ እርስዎንና ልጆችዎን የሚበድል ሰው ቤቱን ለቀ እንዲወጣና/ወይም ከአጠገብዎ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ይሆናል።

ለምሳል፡ ከአጠገብዎ እንዳይደርስ የፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲሰጥ ለማመልከት ልትረዳዎ ትችላለች። በዚህ የፍ/ቤት ትእዛዝ ውስጥ እርስዎንና ልጆችዎን የሚበድል ሰው ቤቱን ለቀ እንዲወጣና/ወይም ከአጠገብዎ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ይሆናል።

- እርስዎን መርዳት ከሚችሉ ሌሎች አገልግሎቶች እንደ በምዕራብ የሴቶች ጤና/Women's Health West ጋር ማገናኘት።

  ለምሳሌ፡ ከሴንተርሊንክ ጋር በማገናኘት ገቢ እንዲኖርዎ ማድረግ፣ ከCentres Against Sexual Assault, children's services, family violence workers እና ከምክር ሰጪ ድርጅቶች ጋር ማገናኘት ይሆናል። ከፈለጉ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እርስዎን በመወከል ልታነጋግርልዎ ትችላለች።
- ለርስዎና ለልጆችዎ ደህንነቱ የተጠበቀ አማካይና ለረጅም ጊዜ የሚሆን መኖሪያ ቤት ማፈላለግና በሚገቡበት ጊዜም መርዳት ይሆናል።
- ረዘም ላለ ጊዜ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ ሊረዳዎ ከሚችል አገልግሎት ሰጪ ጋር ታገናኝዎታለች።



**በአጣዳፊ ችግር ውስጥ ከሆኑ እባክዎ በ000 ለፖሊስ መደወል ይሆናል።**